ኢ.ሀ.ሥ.አ.

# የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።

Ethiopians' Citizen Democratic Union | Union Citoyenne Démocratique des Éthiopiens

www.slttunhzb.net

sh1@ttomar.net

---

ገ_ዐዓ_20160101_ዐማርኛ

## የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ የ 2016 ፡ ዓ.ም. ፡ መልካም ፡ ምኞት ፡ መልእክት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡–

## « ኹሉም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ በሀገራዊነቱ ፡ ዐምሐራ ፡ ነው ! መነሻውም ፡ መድረሻውም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ናት ! »

---

ለንደን ፥ መስከረም ፡ 1 ፡ ቀን ፡ 2016 ፡ ዓ.ም. ።

**የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ !**

የዘመናት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፥ እንኳን ፡ ለ 2016 ፡ ዓ.ም. ፡ በደኅና ፡ አደረሰኽ ፡ እያለ ፥ ውጥን ፡ አካልኽ ፥ **የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ፡ ( ኢ.ሀ.ሥ.አ. )** ፡ ላዲሱ ፡ ዓመት ፡ የድል ፣ የአንድነት ፣ የነጻነት ፡ እና ፡ የሰላም ፡ ምኞቱን ፡ በፍጹም ፡ ትሕትና ፡ ያቀርብልኻል ።

**የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ !**

ከ 1966 ፡ ዓ.ም. ፡ አንሥቶ ፡ ላ 49 ፡ ዓመታት ፡ የተፈራረቁብኽን ፡ የውንብድና ፡ አገዛዞች ፡ ለሰባት ፡ ሱባኤ ፡ ታግሠኽ ፥ እንሆ ፡ በ 50 ኛው ፡ ዓመት ፡ ላይ ፥ ቈርጠኽ ፡ በመነሣት ፥ በኢ..ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ስም ፡ ጠላት ፡ የተከለብኽን ፡ የ"አፓርትሀይድ" ፡ ሥርዐት ፡ በፋኖነት ፡ የዐርበኝነት ፡ ትግል ፡ ለመገላገል ፡ ተቃርበኻል ። የዐላማኽ ፡ ርቱዕነት ፡ እንሆ ፡ ገና ፡ ከኹምሩ ፡ ታላላቅ ፡ ድሎችን ፡ አቀዳጅቶኽ ፥ መደምደሚያውን ፥ እመናገሻ ፡ ከተማኽ ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ በድል ፡ አድራጊነት ፡ ለመግባት ፡ የአርባ ፡ እና ፡ የኀምሳ ፡ ኪሎሜትር ፡ ጕዳይ ፡ ኾኖልኻል ።

ጠላት ፡ ግን ፡ መቼም ፡ ቢኾን ፡ አይተኛልኽምና ፥ ትግልኽን ፡ ጠልፎ ፡ ሊከፋፍልኽና ፡ ድልኽን ፡ ሊያመክንብኽ ፡ ዘወትር ፡ እንደሚጠበብ ፡ ታውቀዋለኽ ። ባንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ መኻከል ፥ ለይቶ ፥ *"የጉራጌ ፡ ሕዝብ" ፣ "የወላይታ ፡ ሕዝብ" ፣ "የሶማሌ ፡ ሕዝብ" ፣ "የትግሬ ፡ ሕዝብ" ፣ "የኦሮሞ ፡ ሕዝብ"* ፣ ወዘተርፈ ፡ ... ፥ የሚለው ፡ በምልክዮሽ ፡ / ፡ በ*"ኢምፔሪያሊዝም"* ፡ ኀይሎች ፡ *መመሪያ* ፡ *መሠረት* ፡ በሰፊው ፡ የሚነዛው ፡ ይሀ ፡ አሳቻ ፡ አባባል ፡–

- ባንድ ፡ ዐምሐራነት ፡ ወይም ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ በነጻ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሕዝብነት ፡ የተዋሐደውን ፡ መላ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሀገራዊ ፡ ሕዝብ ፡ ነጣጥሎ ፡ ትግልኽን ፡ ያዳክምብኻል ፤
- ኢትዮጵያን ፡ የ"ሕዝቦች" ፡ መራኰቻ ፡ አድርጎ ፥ ምልክዮሽ ፡ በ*"አደራዳሪነት"* ፡ እመኻል ፡ ተሠይሞ ፥ አንዱን ፡ ካንዱ ፡ እያገዳደረ ፡ በማናከስ ፥ ሀገሪቱን ፡ ለፍጹም ፡ ጥፋት ፡ ሊዳርግብኽም ፡ ይሰናዳል ።

ለዚህ ፡ አደጋ ፡ መድኀኒቱ ፡ አንድ ፡ ነው ፡– ***ኹሉም ፡ ለኢትዮጵያዊ ፡ ሀገራዊነቱ ፡***

***ወይም ፡ ባንድ ፡ ቃል ፡ ለዐምሐራነቱ ፡ ይታገል !*** ዐምሐራነት ፡ *"ዘር"* ፡ አይደለም ፤ የመሳው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የግብር ፡ ስሙ ፣ ሀገራዊ ፡ ማንነቱ ፡ እንጂ ። መሳ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የእያንዳንዱ ፡ ሀገራዊ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የኾነችውን ፡ ያኽል ፥ እያንዳንዱ ፡ ሀገራዊ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ደግሞ ፡ የመሳ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነው ። የሀገራዊነት ፡ መብታችን ፡ ሲከበር ፥ ሰብኣዊ ፡ መብታችንም ፣ ማኅበራዊ ፡ ማንነታችንም ፣ ማንኛቸውም ፡ አለኝታዎቻችን ፡ ኹሉ ፡ ዐብረው ፡ ይከበራሉ ፤ እነዚህን ፡ የመሳሰሉ ፡ ጸጋዎች ፡ ኹሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ እና ፡ የሕዝቧ ፡ የአንድነቱ ፡ ጸጋዎች ፡ መኾናቸው ፡ አይዘነጋም ።

የኢ..ፌ.ዴ.ሪ.ን ፡ የ"አፓርትሀይድ" ፡ ሥርዐት ፡ ገርስሶ ፡ ለመጣል ፡ እጫፍ ፡ ደርሰኻል ፤ ነጻ ፡ ያወጣኻቸውን ፡ ወረዳዎች ፡ ኹሉ ፡ በመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ የወረዳ ፡ መዋቅርነት ፡ እየደረጀኽ ፥ ሐሳብ ፡ እና ፡ ልብኽን ፣ ዐይን ፡ እና ፡ እግርኽን ፡ ወደ ፡ መናገሻ ፡ ከተማኽ ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ አድርገኽ ፥ መሳ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በፍጥነት ፡ ለመቈጣጠር ፡ ታገል ። ለዚህም ፡ አፈጻጸም ፡ ይረዳኽ ፡ ዘንድ ፥ በሚያዝያ ፡ ወር ፡ 2015 ፡ ዓ.ም. ፡ **ኢ.ሀ.ሥ.አ.** ፡ አስሰናድቶ ፡ ባስተላለፈልኽ ፦

***" ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ ሀገራዊ ፡ ቅያስ ። "***

በተሠኘው ፡ ሰነድ ፡ የሰፈረው ፡ የመፍትሔ ፡ ሐሳብ ፡ ( www.slttunhzb.net ) ፡ የተሟላ ፡ መመሪያ ፡ ይኾንልኻል ፡ ሲል ፡ አንድነታዊ ፡ ውጥን ፡ አካልኽ ፡ **ኢ.ሀ.ሥ.አ.** ፡ ዳግመኛ ፡ በትሕትና ፡ ያሳስብኻል ፤ በትግልኽም ፡ ከጐንኽ ፡ አይለይም ፨

ትሑት ፡ አገልጋይኽ ፦

**ኢ.ሀ.ሥ.አ.**

